"በዚህ አንገብጋቢ ወቅት ለህሊናችን እንቁም!"

እነሆ ኮሮና አንዳችን ካንዳችን ለይቶ አጥቅቷልን? የሆነ ብሄርን ለይቶ አይነካምን ? በፍፁም! እንኳን ኢትዮጵያውያንን መላውን አለም አንድ አድርጎ የለም እንዴ፡፡ ለዚህ ነው ከማንኛውም ጊዜ በላይ ሃገራዊ አንድነት ማጠናከር አለብን የምንለው፡፡ በአንድነት በትብብር ካልሆነ ልንጋፈጠው አንችልም፡፡ ከቻይናውያን የምንማረው መልካም ትምህርት በዚህ ሃገራዊ አንገብጋቢ (national emergency situation) ሁሉም ዜጋ እንደ አንድ ሰው አስበዋል፡፡ የመንግስትን ትእዛዝ ሁሉም በጥብቅ ያከብራል ፤ ምክሮችን በጥብቅ ይተገብራል ፤ አንዱ አንዱን በእጅጉ ያግዛል፤ ይተባበራል፤ ይደጋገፋል፡፡ ለሃገራዊ ተልእኮ ሂድ ወደተባለበት ይሄዳል ፤ በአጠቃላይ በፍፁማዊ ሃገራዊ አንድነት እና በመተባበር ስሜት ይህን በሃገር ላይ የመጣ አደጋ ይከላከላል፡፡ ህዝባችን በእጅጉ መተባበር እና አንድነቱን ማጠናከር በሚፈልግበት በዚህ አንገብጋቢ ወቅት(corporate responsibility ) ህሊናቸውን የሸጡ በህዝባቸው ስቃይ መነገድ የሚፈልጉ ጥቂት ስግብግብ ነጋዴዎች ከቫይረሱ ባሻገር የዋጋ ጭማሪ በማድረግ ህዝቡ ላይ ስቃይ ለማብዛት መሻት በእጅጉ ከኢትዮጵያዊ ጨዋነት የወረደ ተግባር በመሆኑ ከዚህ ድርጊታቸው በፍጥነት እንዲታቀቡ እንመክራለን፡፡ በዚህ መንገድ የመጣ ትርፍ ለራስም ለህሊናም ለሃገርም እዳ ነው፡፡ በወገን ስቃይ የሚበላ እንጀራም የግፍ እንጀራ ነው፡፡ ሁላችንም በዚህ አጋጣሚ በቻልነው ሁሉ መንግስት ያወጣቸውን መመሪያዎች እና የጥንቃቄ መልእክቶች በሙሉ ልብ መተግበር ፤ እንዲሁም ሌሎችን ማገዝ አስፈላጊ መሆኑን አንዘንጋ ፡፡ በትራንስፖርት መጨናነቅ ሊኖር የሚችለውን የበሽታው መተላለፍ ለመቀነስ በቻልነው አቅም መኪና ያለን ሌሎችን በማገዝ ፤ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ማግኘት ለማይችሉ በማቅረብ፤ ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎችን ሁሉ በቻልነው በመለገስ አንድ ሆነን ይህንን ወቅት ልንጋፈጠው ይገባል፡፡ ኢትዮጵያዊ አንድነት ንፋግነት አይደለም ፤ ለሌሎች ማሰብና መተባበር ነው! ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን ይጠብቅ!

አቶ ተስፋዬ በልጅጌ የአዲስ አበባ ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ እና የብልፅግና ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ አባል